# የኢየሱስ ታሪኮችን ንገሩን

ካህን ኒል ኤል አንደርሰን
የአስራ ሐለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

ፕሬዘደንት ሞንሰን እንደ አስራ ሑለት ሐዋሪያት ሸንጎ አባል እንድሆን ከጠሩኝ አንድ አመት አልፏል። አዳኝን ሁልጊዜም እወደዋለሁ፣ ነገር ግን ለእርሱ ጥሩነት እና ታላቅነት እና በእኔ ላይ ባለው ተፅዕኖ ምስጋና ያለኝ አምልኮት በግልና በተቀደሰ መንገድ እያደገ መጥቷል። በግርማዊው ትንሳኤው እና ህያው እንደሆነ ባለን እርግጠኛ እውቀትም ከእናንተ ጋር እደሰታለሁ።

ፕሬዘደንት ሞንሰን ይህን ትውልድ "ከሁሉም እንደተሻሉ"1 ገልጸዋቸዋል እና ለወጣቶቻችንንም "በሚያስገርም ጊዜ ወደምድር መጥታችኋል። በፊታችሁ የሚገኘው እድልም መጠን የሌለው ነው" ብለዋቸዋል።2 ነገር ግን እንዲህም አስጠንቅቀዋል፣ "በአስቸጋሪ ጊዜ ነው በምድር ላይ የተላክነው።"3 "ይህን ታዛዥ ያለመሆን እና የእግዚአብሔርን ህግጋት በተራ የሚልቁበት ዘመን ነው።"4 ትኩረታችንን ሊወስድብን በሚችሉ ነገሮችም ተከብበናል። "ጠላትም በውሸቱ ሊጠምደን ዘንድ የሚችላቸውን ነገሮች በሙሉ ይጠቀማል።"5

ለሚመጡት ትውልዶች ሀላፊነት አለን። ወደዚህ ምድር በአስፈላጊ ሀላፊነት እና ታላቅ መንፈሳዊ ችሎታ መጥተዋል። በምናዘጋጃቸው ሀላፊነትም ችላ ማለት አንችልም። እንደአስተማሪዎች እና ወላጆች ያለብን ፈተና ቢኖር የመንፈሳዊ መሰረት በነፍሳቸው ውስጥ ማስገኘታችን ሳይሆን ከዚህ ህይወት በፊት የነበራቸውን መንፈሳዊነት ለማሳደግ እንዲቀጥሉ ማድረጉ ነው።

በዚህ ከሰአት በኋላ፣ በመጀመሪያ ክፍል መዝሙር ላይ ያለውን ልመና ለማጉላት እፈልጋለሁ።

በዚህ ቢገኝ ኖሮ የምጠይቀውን
የኢየሱስን ታሪኮች ንገሩኝ፣ ላዳምጣቸው እወዳለሁ።6

ዛሬ በአለማችን፣ እያንዳንዱ ልጅ፣ እያንዳንድ ወጣት ወንድ እና ሴት ወደ እውነት የምትቀየርበት ወይም የሚቀየርበት ያስፈልገዋል። እያንዳንዱም ከወላጆች፣ ወጣት መሪዎች፣ እና ከደጋፊ ጓደኞች የተለየ የራሳቸው ብርሀን እና በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ቋሚ እና የማይነቃነቅ እምነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል።

የኢየሱስ ታሪኮች በልጆቻችን ልቦች ውስጥ እምነትን ሊያሳድጉ ይችላሉ። ኢየሱስ እንዳለው፣ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ።"ተደጋግሞ የሚካፈል የኢየሱስ ታሪክ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን ያመጣል እና የምስክር መሰረtንም ያጠናክራል። ለልጆቻችን የምንሰጣቸው ከዚህ የበለጠ ስጦታ አል?

የክርስቶስ ህይወት እና ትምህርቶች በልጆቻችን አዕምሮዎች እና ነፍሶች ላይ ተቀርጸዋል? በህይወታቸው ምን እንደሚያደርጉ በሚያስቡበት ጊዜ ስለአዳኝ ህይወት ያስባሉ? ወደፊት በሚመጡት አመቶች ይህ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

ከሁሉም ታላቅ የሆነው ኢየሱስ ከዚህ ህይወት በፊት በነበረው ሸንጎ ላይ “እዚህ አለሁ፣ እኔን ስደደኝ” ያለበትን በአዕምሮአቸው ያዩታል።9 ለማገልገ ያላቸውን ፍላጎት የእርሱን ምሳሌ እንደመከተል ይመለከቱታል?

ስለትሁት መወለዱ ያስባሉ? የአለም አዳኝ “በግርግም ውስጥ ተኝቶ”።10 የንብረት ባለቤት መሆንን በደንብ እንዲያውቁ ዘንድ የእርሱ ሁኔታ ይረዳቸዋል።

ኢየሱስ በየጊዜ “ጠይቁ እናም ታገኛላችሁ” ብሎ እንዳስተማረ ያውቃሉ?11 ስለእራሳቸው ችግስ ተንበርክከው በሚጸልዩበት ጊዜ የምስጋና ጸሎቱ እና ወደ አባቱ ያቀረበው ልመናዎች በልጆቻችን አዕምሮ ያልፋሉ?

ኢየሱስ ለጆች ስላለው ፍቅር፣ እንዴት በእጆቹ እንዳቀፋቸው፣ እንደጸለየላቸው፣ እና እንዳለቀሰ ነግረናቸዋል? እነርሱን “ለመቀበል ክንዶቹን ዘርግቶ” እንደሚጠብቅ ልጆቻችን ያውቃሉ?

ስለጾም ህግ ስናስተምራቸው፣ ኢየሱስ በጾመበት ታሪክ ጥንካሬ ያገኛሉ?

አዳኝ ጓደኞቹ ትተውት ሲሄዱ እና ሐዋሪያቱን “እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?” ብሎ ሲጠይቅ የተሰማውን ብቸኝነት ልጆቻችን ያውቁታል?

የአዳኝን ታምራት ሀይል ልጆቻችን ተሰምቷቸዋል? የስጋ ደዌ በሽታ ያለውን ፈወሰ፣ እናም ለአይነ ስውርም አይኑ እንዲያይ አደረገ። 5000ን መገበ፣ ባህርን ጸጥ አደረገ፣ እና አላዛርን ከሞት አስነሳ። “ተአምራት የሚከናወኑት በእምነት” እንደሆነ ልጆቻችን ያምናሉ እና በህይወታቸው ውስጥም ለታምራት ይጸልያሉ?

አዳኝ ለምኩራብ አለቃ “እመን ብቻ እንጂ አትፍራ” ባለበት ብርታትን አግኝተዋል?

ልጆቻችን ስለፍጹም ህይወቱ፣ ስለእራሳ ሳያስብ ስላገለገለበት፣ ስለተከዳበት እና ስለተሰቀለበት ያውቃሉ? ስለትንሳኤው እርግጠኛነት፣ ኔፊያውያንን በአሜሪካ እንደጎበኘ፣ በቅዱስ ጥሻ ውስጥ ለነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንደታየ ምስክራችንን ሰጥተናቸዋል?

ሁሉም ትክክል በሚደረጉበት፣ እና እያንዳንዱም ጉልበቶች በሚንበረኩበት፣ እና እያንዳንድ ምልሳትም እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የሚመሰክርበትን በግርማ የሚመለስበትን በጉጉት ይጠብቃሉ?

ልጆቻችን “ልሰማይ የምወደውን የኢየሱስ ታሪክ ንገሩኝ” ብለው ይጠይቃሉ?16

ለወጣቶች እና ለልጆች፣ ለአስፈላጊ ሀላፊነት እና ታላቅ መንፈሳዊ ችሎታ ኑሩ። ስለኢየሱስ በተጨማሪ ለማወቅ ፈልጉ፣ ቅዱስ መጻህፍትን ክፈቱ። አንዱ ሀሳብ ቢኖር መፅሐፈ ዮሀንስን አንብቡ እና ከወላጆቻችሁ እና እርስ በራስም ተወያዩባቸው።

ለአባቶች እና ለእናቶች፣ ለአያቶች፣ እና የእራሳቸው ልጆች ባይኖራቸውም ልጆችን እና ወጣቶችን በፍቅር ለሚንከባከቡ ሁሉ ምክሬ ቢኖር ስለኢየሱስ ክርስቶስን በየጊዜም እንዲናገሩ ነው። በቅዱስ ስሙም ታላቅ መንፈሳዊ ሀይል አለ። "በክርስቶስ እና ሁሉን በሚችለዉ ጌታ ስም ካልሆነ በስተቀር ለሰው ልጆች ደህንነት ሊመጣ የሚችልበት ሌላ ምንም የተሰጠ ስም፣ መንገድ፣ እና ዘዴ የለም።"17

ልጆቻቸውን በቤት አባት በማይኖርበት የሚያሳድጉ ብዙ እናቶ ቻሉ። ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስትናገሩ፣ የሰማይ ሀይል ሲባርካችሁ እንደሚሰማችሁ የተስፋ ቃል እሰጣችኋለሁ።

ባለቤታቸው ከሞቱ ባኋላ፣ እህት ስቴላ ኦክስ ካህን ዳለን ኤች ኦክስ በተጨማሪ ሶስት ልጆቻቸውን ብቻዋን አሳድገዋቸዋል። አንድ ጊዜም እንዲህ አሉ፣ "ጌታ እንደሚወደኝ እና ለሀላፊነቴ ብቁ እንደምሆን እንዳውቅ ተደርጌአለሁ። የምታቀፍበት ፍቅር ተሰማኝ እና በሚመጡት ፈተናዎች እንደሚደግፈንም ተሰማኝ።"18

ለአባቶች ልዩ ምክን ለመስጠት እፈልጋለሁ፤ ስለአዳኝ ለልጆቻችሁ የመንገር ዋና ክፍል ሁኑ። ከእናታቸው ጋር የእናንተን የእምነታችሁ ማረጋገጫ መግለጫ ይፈልጋሉ።

ምንም እንኳን ልጅ በሚያምን ልብ የማያዳምጡበት ጊዜ ቢኖርም፣ ስለኢየሱስ የምትሰጧቸው ምስክር በነፍሳቸው እና በልባቸው ውስጥ ይቀራሉ። ትክክል ያልሆነውን መንገድ ስለመረጠው አልማ ታሪክ ታስታውሳላችሁ? ሲመለስም እንዲህ አለ፣ "የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተባለው፣ የዓለምን ኃጢአት ለመክፈል ስለሚመጣው፣ የአባቴን ትንቢት መስማቴን አስታወስኩኝ።

"እንግዲህ፣ አዕምሮዬ እርሱን በማሰብ በተያዘበት ጊዜ፣ በልቤ እንዲህ በማለት አለቀስኩ፥ የእግዚአብሔር ልጅ የሆንክ ኢየሱስ ሆይ፣ ምህረትህ በእኔ ላይ ይሁን…።"19

ልጅ የማይሰማ ከሆነ፣ አትጨነቁ። ጊዜ እና እውነት በእናንተ በኩል ነው። በትክክለኛው ጊዜ፣ ቃላቶቻችሁ ከሰማይ እንደመጡ አይነት ተመልሰው ይመጣሉ። ምስክራችሁ ልጆቻችሁን አይተዋቸውም።

መበኪና ውስጥ፣ በአውቶባስ ላይ፣ እራት ስትበሉ፣ ለጸሎት ስትንበረከኩ፣ ቅዱስ መጻህፍትን ስታጠኑ፣ ወይም በምሽት ንግግራችሁ ስለአዳኝ በአምልኮ ስትናገሩ፣ ቃላቶቻችሁን የጌታ መንፈስ ያጅባል።

የምትችሉትን ስታደርጉ፣ የኢየሱስ ምስክር በልጆቻችሁ ልቦች ላይ በቀስታ ይገባሉ። ወደሰማይ አባታቸው በትሁትነት በጸሎት ይሄዳሉ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል ተፅእኖው ይሰማቸዋል። በኢየሱስ ክርስቶስ ጠንካራ የግል እምነት በእርግጥም ወደፊት ለሚያጋጥማቸው ፈተና ያዘጋጃቸዋል።

በBYU ተማሪዎች እያለን ከ ቢል ፎረስተር እና ከደቢ ሀቼንግስ ጋት ተገናኘን። ቢል ከሚስዮን ተመልሶ የመጣ ነበር። እርሱ እና ደቢ በኦክላንድ ቤተመቅደስ ተጋቡ። በሜሳ አሪዞናም መኖር ጀመሩ እና በአምስት ወንድ ልጆች እና ሁለት ሴት ልጆች ተባረኩ። ቢል እና ደቢ ልጆቻቸውን እነርሱ እንደሚወዷቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲወዱ አስተማሯቸው። በኦአክሳካ ሜክሲኮ ሚስዮን የሚያገለግለው ካህን ዳነል ፎረስተር እንዲህ ብሏል፣ “በየቀኑ በምንም ሳናቆም ከትምህርት ቤት በፊት ቅዱስ መጻህፍትን እያነበብን እንወያይ ነበር።”

አሁን አግብታ ሁለት ልጆች የወለደችው ሴት ልጃቸው ካራ በጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሲወስዳት እንደነበረ ታስታውሳለች። እንዲህም አለች፣ “አባቴ ንግግሮችን፣ ቅዱስ መጻህፍታትን እና ገጠሞችን መገምገም ይወድ ነበር እና በዚህ በጠዋት በምንጓዝበት ጊዜ የገመገምናቸውን ለማስታወስ እንሞክር ነበር።” አንዱ የሚወደው ቅዱስ መጻህፍት ይህም ነበር፤ “አስታውሱ፣ አስታውሱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በክርስቶስ፣ አዳኝ በሆነው በዓለቱ መሰረታችሁን መገንባት እንዳለባችሁ፤ ዲያብሎስ ኃይሉን …በአውሎ ነፋስ እንደሚወረወር ዘንጉን በላከ ጊዜ፤ አዎን ትክክለኛ መሰረት በሆነው ሰዎች ከገነቡበት ሊወድቁበት በማይችሉበት አለት ላይ ስለገነባችሁ … ጎትቶ ለመጣል ኃይል አይኖረውም።”20

ከትንሳኤ ከመሆኑ 3 ቀን በፊት በ2000 ዓ/ም ቢል ፎርስተር እንደ Estate Groves Ward ኤጲስ ቆጶስ ያገለግል ነበር። እቤት ከመድረሱ ከ2 km በፊት መኪናው በትልቅ መኪና ተመታ። ደቢና ልጆቹ ከእርሱ በኋላ ከቤት ወጥተው በአደጋው ላይ ደረሱ። ቢል ከአዳጋው አልዳነም ነበር። የውድ አባታቸው እና ባለቤታቸው የማይሞተው መንፈሱም ሞትን ወዳሸነፈው የእግዚአብሔር ልጅ ሄደ።

ደቢ እና ሰባት ልጆቿ የሚያስፈልጋቸውን ጥንካሬ እንዴት አገኙ? በአባቷ አደጋ ጊዜ 15 አምቴ የነበረችው ካራ ይህን ነገረችኝ፤ “አባቴ እና እናቴ ስለአዳኝ እንድማር ላደረጉበት ዘዴ ምስጋና ይሰማኛል። ቅዱስ መጻህፍትን ከእኔ ጋር አነበቡ፣ ከእኔም ጋር ጸለዩ፣ በአዳኝ ልግስና፣ ፍቅር፣ እና ትእግስትም ምሳሌ ነበሩ።…ስለአዳኛችን ህይወት፣ ሚስዮን፣ እና ከሞት መነሳት ሳስብ፣ የትንሳኤ ቀን በህይወቴ በጣም ሆዶ ባሻ ነኝ፣ እና ስለምድር አባቴ ህይወትም አስታውሳለሁ።”

ካህን ዳንኤል ፎርስተርም እንዲህ አለ፣ “አባቴ ሲሞት አስር አመቴ ነበር። ይህም አስቸጋሪ ጊዜ ነበር…እናቴ ሁልጊዜም የአዳኝ ትምህርት ምሳሌ ነበረች። ከእኔም ጋር አባቴ በሚስዮን የነበረው የስም ምልክቱን ይዜ ሄጃለሁ። አባቴ መጥቀስ የሚወዳቸው ሁለት ነገሮች ፤ ‘አንደኛው ጌታ እስከሆነ ድረስ ሁለት ሰዎች ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላሉ’ እና ‘አዳኝ መሰረታችን መሆን አለበት። ያለእዚያም እንታገላለን” ነበሩ።

የፎረስተር ልጆች ልቦች በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ተሞልተዋል። በዚህ በትንሳኤ ቀናት፣ አባታቸው ከሞተ ከ10 አመት በኋላ፣ በዝልቅ ይናፍቁታል፣ ነገር ግን የመሞቱ ሀዘን ግን በክርስቶስ የተሸፈነ ነው። 21 በክርስቶስ መመዘን በማይቻለው ስጦታ ምክንያትም ከምድር አባታቸው እና ከሰማይ አባታቸው ጋር እንደገና ለመሆን እንደሚችሉ ያውቃሉ።

የኢየሱስ ታሪኮችን ንገሩኝ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከእግዚአብሔር ነብይ እንሰማለን። ስለነብዩ ሲናገርም ጌታ እንዲህ ብሏል፤ "ቃሉን ልክ ከእኔ አፍ እንደወጣ አድርጋችሁ ትቀበላላችሁ።"22 ፕሬዘደንት ቶማን ኤስ ሞንሰን የጌታ ቃል አቀባይ እንደሆኑ እመሰክራለሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የሰው ዘር ሁሉ አዳኝ እንደሆነ እመሰክራለሁ። ህይወቱ፣ የኃጥያት ክፍያው፣ ትንሳኤው፣ እና የምንጠብቀው ዳግሞ መመለሻው እንደ ጸሀይ መውጣት እርግጠኛ ናቸው። ስሙም ለዘለአለም ይሞገስ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስም፣ አሜን።